ማብራሪያዎቹ በስፋት ከሊቃውንቱ የተወሰዱ በመሆናቸው ከዚህ ባለፈ ቀጥታ ራሳቸውን መጽሃፍቶች ብታነቧቸው እጅጉን ትጠቀማላችሁ። ለአሁኑ ግን እኔ አንዱን ለመምረጥ ያህል በpdf ቀጥታ የምታገኙበትን ቦታ ልጠቁማችሁ፡

- ✓ Origen (ኦሪገን ወይም አርጌንስ) ዘፍጥረትን የተረጎመበትን ድርሳን(Homilies on Genesis) እዚህ ማብራሪያ ላይም ብዙ ጊዜ አካተነዋል በተለይ መንፈሳዊ ትርጓሜዎቹ ድንቅ ናቸው፤ ኢንተርኔት ላይ ቢኖርም በቀላሉ ላታገኙ ስለምትችሉ ከሥር ያለውን ሊንክ በመጫን በቀላሉ መጽሃፉን አውርዱት፡ http://www.mediafire.com/file/132f8fc3f8x981r/origen-homilies-on-genesis-and-exodus-_-_%255Bchristianlib.com%255D.pdf/file

# ኦሪት ዘፍጥረት

- ❖ እብራይስጡ 'Bereshit' ይለዋል "በመጀመሪያ" ማለት ሲሆን በግሪክ ሰባ ሊቃናቱ(Septuagint) Genesis ይለዋል "ልደት፤ መጀመሪያ ወይም መገኛ" እንደ ማለት ነው።

## ምዕራፍ አንድ

1. እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰማይና ምድርን ፈጠረ።
   - እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰማይን እንደ ጣርያ ከላይ፤ ምድርን እንደ መሰረት ከሥር አድርጎ ፈጠራቸው። "ሰማይና ምድርን ፈጠረ" ሲል ያስቀደመው ምድርን ሳይሆን ሰማይን ነውና አስቀድሞ እግዚአብሔር አምላክ ሰማይን(ከነ ሰራዊቱ) ከዛም ምድርን ፈጠረ።
     ቴዎፍሎስ ዘአንጾኪያ[1] እግዚአብሔር ሰማይን እንዳስቀደመ ሲናገር እግዚአብሔር ከእኛ ሃሳብ በላይ ሁሉን ቻይ እንደሆነ ያሳያል ይላል። ሰው ቤቱን ሲሰራ አስቀድሞ መሰረት ያቆማል ከዛም ጣርያውን ያበጃል፤ እግዚአብሔር ግን አስቀድሞ ጣርያውን ሰርቶ ወደ ምድር ወረደ። "በሰው ዘንድ የማይቻለው በእግዚአብሔር ዘንድ ይቻላል"[2] እንዲል።
   - ባስልዮስም[3] የስድስቱ ቀናት ስነ ፍጥረት ላይ በጻፈው ድርሳን.. "በመጀመሪያ" ብሎ ሰማይና ምድር መጀመሪያ እንዳላቸው ተናገረ አስጀማሪያቸው(ፈጣሪያቸው)ም እግዚአብሔር እንደሆነ ገለጠ። አንድም የፍጥረት መጀመሪያ አደረጋቸው። በማለት "ምድር ከዘላለምም አለች" ለሚሉ ፈላስፎችና አህዛቦች ያስረዳል። ዮሃንስ አፈወርቅም[4] ዘፍጥረትን ሲተረጉም ይህንኑ ሃሳብ ያጠናክራል።
   - አንድም አሪገን[5] "በመጀመሪያ" የሚለውን ሲያብራራ "የሁሉ ነገር መጀመሪያ ጌታችን ኢየሱስ ካልሆነ ሌላ ምንድነው? በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ የተፈጠሩ ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኩር የሆነ እርሱ ነው።[6] 'በመጀመሪያ' ሲል በቃሉ ማለት ነው። እግዚአብሔር በቃሉ ሰማይና ምድርን ፈጠረ እንደማለት። ዮሃንስም በወንጌሉ 'በመጀመሪያ ቃል ነበር፤ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበር። ይህም በመጀምሪያ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር። ሁሉ በእርሱ ሆነ፤ ከሆነውም ሁሉ ያለእርሱ ምንም የሆነ የለም።' እንዲል" በማለት በመጀመሪያ ማለት በመጀመሪያ በነበረው ቃል በልጁ ፈጠረ ማለት ነው ይላል። በእርግጥ ተወዳጅ ሃዋርያም "በዘመን መጨረሻም <u>ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ</u> ተናገረን" እንዲል።[7]

2. ምድርም ግን ባዶ ነበረች አትታይምም[8] ነበር። የተዘጋጀችም አልነበረችም። ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውኃው ላይ ይሰፍፍ ነበር።
   - ምድር አትታይም ነበር፤ አዝርእትን ለማብቀል አመቺ ሆና ገና አልተዘጋጀችም ነበርና ነው፤ በውኃ የተሸፈነች ነበረች፣ ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበር እንዲል ምድር አትታይም ነበር።[9]
   - "የእግዚአብሔር መንፈስ በውኃው ላይ ይሰፍፍ ነበር" የተባለው መንፈስ ቅዱስ ነው። ስነ ፍጥረት ላይ ሥላሴ(አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ) ተገለጡ። አስቀድሞ "እግዚአብሔር(አብ) በመጀመሪያ(በወልድ) ሰማይና ምድርን ፈጠረ" ብሎን ነበር አሁን ደግሞ "የእግዚአብሔርም መንፈስ በውኃው ላይ ይሰፍፍ ነበር" አለን።

---

[1] To Autolycus 2:8 remarks on the creation of the world
[2] ሉቃ 18፡27
[3] Hexaemeron(the six days) 1፡3
[4] Hom. 2:10
[5] Hom. On genesis 1
[6] ቆላ 1፡15
[7] ዕብ 1፡2
[8] "አትታይም" የሚለው በግሪክ ሰባ ሊ. ላይ ይገኛል። የፕሮቴስታንቱ መጽሃፍት ላይ የለም።
[9] Hexaemeron 2:1

- "ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግስት ሊያይ አይችልም" እንዲል ጌታ ኢየሱስ በወንጌል፤ እዚህም ጋር መንፈስ በውኃው ላይ መስፈፉ የጥምቀት ምሳሌው ነው።
- የኢየሩሳሌሙ ቄርሎስ ስለ ጥምቀት በጻፈበት ድርሳኑ እንዲህ አለ፡ "ውሃ የዓለም ጅማሬ ነበር፤ ዮርዳኖስ(ጥምቀት) ደግሞ የወንጌል" አስከትሎም እንዲህ አለ፡ "እስራኤል ከፈርኦን(ባርነት) ሲለይ በባህር እንደሆነ፤ ዓለም ደግሞ ከሃጢዓት(ባርነት) በጥምቀት ይለያል።"[10]

3. እግዚአብሔርም ብርሃን ይሁን አለ፤ ብርሃንም ሆነ።
   - ይህ ብርሃን የጸሃይ ብርሃን አይደለም፤ ጸሃይና ጨረቃ ፍጥረታቸው አራተኛው ቀን ላይ ነውና። ይህ ብርሃን እንዴት ያለ ብርሀን እንደሆነና ልክ የጸሃይና ጨረቃ ብርሃን በ1 ቀን 24 ሰዓት እንደሚያስቆጥሩት የዚህን ብርሃን ግን 1 ቀን ሲል በጸሃይና ጨረቃ አቆጣጠር ምን ያህል ቀን ወይም አመት እንደሆነ ልናውቀው አንችልም።
   - አለም አዲስ ሆና ስትፈጠር ብርሃን ይሁን አለ፤ በጥምቀት እንደ አዲስ ስንፈጠር ብርሃን እንደሚሆንልን።
4. እግዚአብሔርም ብርሃኑ መልካም እንደሆነ አየ፤ እግዚአብሔርም ብርሃኑን ከጨለማው ለየ።
   - ቅዱስ ባስልዮስ "እግዚአብሔር 'መልካም እንደሆነ አየ' ሲባል እግዚአብሔር ነገሮችን አይቶ አሽትቶ እንደሚያደንቅ የተነገር አይደለም። ይልቁንም እርሱ እንደወደደው እንደፈቀደው መፈጠሩንና ለወደፊትም ደግሞ ለእኛ ለምንጠቀምበት መልካምና ጠቃሚ እንደሆነ ሲያመለክት ነው" በማለት ይናገራል።[11] ብርሃኑን ከጨለማው ለየ ሲልም እንዳይቀላሉ አንዱን የአንዱ ተቃራኒ አድርጎ ለያቸው ሲል ነው።
   - አስቀድመን ጨለማ የነበርነውን እኛን በጥምቀት ልጆቹ አድርጎ ብርሃኑን በውስጣችን በማብራት ከጨለማው እንደለየን "ብርሃኑን ከጨለማው ለየ" ብሎ ይናገራል።
   - አንድም ብርሃናዊ መላእክትን ከወደቁት መላእክት ለየ። ጨለማ አላቸው፤ ክብርን ፈልገው ከወደቁ በኋላ ጨለማን ለብሰው ብርሃናዊነትን አጥተውታልና። አሁን ሰይጣን የብርሃን መላእክትን እስኪመስል ራሱን ይለውጥ ይሆናል እንጂ እርሱስ ጨለማ ነው።[12]
5. እግዚአብሔርም ብርሃኑን "ቀን" ጨለማውንም "ሌሊት" ብሎ ጠራው። ማታም ሆነ፤ ንጋትም ሆነ፤ አንድ ቀን።
   - በአይሁድ የቀን አቆጣጠር ቀኑ የሚጀምረው ከማታ ነውና "ማታም ሆነ" ብሎ ጀምሯል።
   - በመጀመሪያው ቀን በአጠቃላይ 7 ፍጥረታት ተፈጥረዋል።[13] (ነፋስ፣ እሳት፣ ውሃ፣ መሬት፣ ጽልመት መላእክት እና ብሩህ ሰማይ ናቸው) ምነው ታድያ ሁሉን በዝርዝር አልተናገረው ካልን፡ አንድም ሁሉ በሰማይና በምድር የሚጠቀለል ነውና አንድም ደግሞ ሙሴ ሲጽፍ ለጊዜው የሚታይ የሚታያቸውን ገልጦ ጻፈላቸው።
6. እግዚአብሔርም በውኃው መካከል ጠፈር ይሁን፤ በውኃና በውኃውም መካከል ይለይ አለ። እንዲሁም ሆነ።
   - በምድር ላይ የነበረውን ውኃ ይከፍል ዘንድ እግዚአብሔር አምላክ ባወቀ ጠፈር ለአይን ማረፊያ ምቹ ሆኖ ተፈጠረ።
7. እግዚአብሔርም ጠፈርን አደረገ፤ ከጠፈር በላይና ከጠፈር በታች ያሉትንም ውኆች ለየ።

---

[10] St Cyril of Jerusalem, Cat. Lect. (on baptism) 3:5

[11] Hexaemeron 3:10, 2:7

[12] 2ቆሮ 11፡14

[13] ኩፋሌ 2፡8

- ከላይ ያለው ውሃ የሕይወት ውሃ ምሳሌ እሱም አማኞች የሚቀበሉት መንፈስ ቅዱስ ነው፤ "በእኔ የሚያምን መጽሃፍ እንዳለ የሕይወት ውሃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል" እንዲል ጌታ በወንጌሉ፤[14] በታች በጥልቁ ያለው ውሃ የቀደመው እባብ ዘንዶው የተጣለበት የጥልቁ ምሳሌ[15] ይሆንና ሃዋርያው ጳውሎስ "እኛስ ሃገራችን በሰማይ ነው" እንዲል ሁለቱን ውኖች የከፈለውን ሰማይ በመሆን ማንም ሰው ራሱን ከምድራዊው ውኃ ከጥልቁ እየለየ በላይ በሰማይ ካለው ውሃ ጋር ባገናኘ ቁጥር ሰማያዊ እየሆነ ከምድራዊ ነገር እየራቀ ሃሳቡና መሻቱ ሁሉ ከምድራዊ ነገሮች እየተለየ ጌታ ኢየሱስ በአባቱ ቀኝ ስለተቀመጠበት ስለ ላይኛው ሰማይ ይሆናል። "እግዚአብሔርም መልካም እንደሆነ አየ" እስኪባልለት ድረስ ወደ ማልካምነት ወይም ፍጹምነት ያድጋል ይለናል አሪገን።[16] በአጭሩ በታች ያለውን ውኃ የኃጢዓት ምሳሌ እንደሆነ ያሳያል ማለት ነው። መዝሙረኛውም "አቤቱ ውኃ እስከ ነፍሴ ደርሶብኛልና አድነኝ። በጥልቅ ረግረግ ጠለቅሁ ኃይልም የለኝም፤ ወደ ጥልቁ ባሕርም ደረስሁ ማዕበሉም አሰጠመኝ"[17] እንዳለው። ውኃ አንድ ጊዜ የጽድቅ የጸጋ ሌላ ጊዜ ደግሞ የኃጢዓት ምሳሌ መሆኑ ሊገርመን አይገባም፤ ምሳሌ ምሳሌ እንጂ እውነታው ራሱ ስላልሆነ አንዱ ነገር ለተለያየ ነገር ሊመሰል ይችላል። "አንበሳ" ለኢየሱስም፤ ለዲያቢሎስም[18] ምሳሌ እንደሆነ ማለት ነው። ሰማያዊ ሰው በታች በምድር ያለውን ውኃ በላይ ካለው ውኃ ይከፍላል ይለያል።

8. እግዚአብሔር ያን ጠፈር "ሰማይ" ብሎ ጠራው። እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደሆነ አየ።[19] ማታም ሆነ፤ ንጋትም ሆነ፤ ሁለተኛም ቀን ሆነ።
   - አስቀድሞ የፈጠረው ሰማይና አሁን ላይ ሰማይ ብሎ የጠራው ጠፈር ይለያያል። ይህ ሰማይ(ጠፈር) በውኃና ውኃ መካከል ያለ ነው። አንዳንድ ሰዎች ጠፈሩን አዕዋፍ የሚበሩበትን ነው ብለው የሚያስቡ አሉ። በውኃና በውኃ መካከል የከፈለውም በላይ ደመናን በታች ደግሞ ምድር ላይ ያለውን ይላሉ፤ ግን ስህተት ነው ከደመናው በላይ ያለውስ ሌላ ጠፈር ሊባል ይሆን? ጠፈር የተባለው ወደ ላይ ስንመለከት የምናየው ሰማያዊውን ጠፈር ማለቱ ነው። ከሱ በላይ ውሃ አለ፤ ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት "ሰማየ ሰማያት፤ **ከሰማያት በላይ ያለ ውኃም** ያመሰግኑታል"[20] ሲል ከሰማያት በላይ ያለ ውኃ የተባለው ይህ ውኃ ነው። ከዚህ ጠፈር ሰማይ በታችም በምድር ላይ ደግሞ ውሃ አለ። ደመናው ግን እዚሁ ምድር ላይ ካለው ወኃ ላይ በመትነን በጋዝ መልክ አየር ላይ ሲቀመጥ ነው 'evaporation' የምንለው ነው፤ ይሄው ራሱ ደግሞ ከጋዝነት ወደ ፈሳሽነት ተመልሶ ይዘንባል 'condensation' ማለት ነው፤ ስለዛ በሁለቱ መካከል የተከፈለ ነገር የለም ብቻ ግን circulate ያደርጋሉ።
   - ቀን ሁለት ፍጥረት ስምንት። (በዚህ ቀን ጠፈር ብቻ ተፈጠረ)
9. እግዚአብሔርም "ከሰማይ በታች ያለው ውኃ በአንድ ስፍራ ይሰብሰብ፤ የብሱም ይገለጥ" አለ፤ እንዲሁም ሆነ። ከሰማይ በታች ያለው ውኃም በመጠራቀሚያው ተሰበሰበ፤ የብሱም ተገለጠ።
   - ውኃውን ከደረቁ የብስ ለየ።

---

[14] ዮሃ 7:38
[15] ራዕ 12:9፤ ራዕ 20:3፤ ማቴ 25:41
[16] On Genesis hom. 1: 2
[17] መዝ 68:1-2
[18] ራዕ 5:5 እና 1ጴጥ 5:8
[19] እግዚአብሔር ከፈጠረ በኋላ ሁሉም ላይ "እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደሆነ አየ" በማለት ሁሉም ውብ ሆኖ በአምላክ ፍቃድ እንደተፈጠረ ይናገራል። የጠፈሩ መፈጠር ላይ ግን "እግዚአብሔርም መልካም እንደሆነ አየ" የሚለው ቃል ተለይቶ በፕሮቴስታንቱ መጽሃፍ የለም።
[20] መዝ 148:4

- ኦሪገን[21] አሁንም ዘፍጥረትን በተረጎመበት ድርሳኑ ላይ መንፈሳዊ ትርጓሜውን እንዲህ በማለት ያስቀምጣል፡ የብሱ ከሰማይ በታች ባለው ውኃ በተሸፈነበት ጊዜ እንዳልተገለጠ፤ ሰውም በዚህ ምድራዊ ውሃ(ሃጢዓት) ከተሸፈነ የብሱ ሊገለጥ ወደ ብርሃንም ሊወጣ አይችልም፤ ምክንያቱም "ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላልና፥ ሥራውም እንዳይገለጥ ወደ ብርሃን አይመጣም"[22]። እንግዲህ ሽፍኖ የያዘንን ከሰማይ በታች ያለ ውሃ(ሃጢዓት) ከላያችን ላይ እናስወግድ የብሳችንም ይገለጥ። በእግዚአብሔር ፊት የሚገለጠው ኃጢዓቱ ከላዩ ላይ የተነሳለት ሰው ነው፤ "የእግዚአብሔር ዓይኖቹ ወደ ጻድቃኑ፤ ጆሮዎቹም ወደ ልመናቸው ነው"[23] እንዲል።

10. እግዚአብሔርም የብስን "ምድር" ብሎ ጠራው፤ የውኆችንም ማጠራቀሚያ "ባህሮች" ብሎ ጠራው። እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደሆነ አየ።
   - ያ ደረቁን የብስ "ምድር" ብሎ ጠራው። ይህንን ምዕራፍ ስንጀምር "እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰማይና ምድርን ፈጠረ።" ብሎን ነበር፤ አሁን ደግሞ ጠፈርና የብስን ሰራና ጠፈሩን አስቀድሞ በፈጠረው ሰማይ ስም ሰየመው፤ የብሱንም አስቀድሞ በሰራው ምድር ስም አዝርእትን ለማብቀል እንዲችል አድርጎ "ምድር" ብሎ ጠራው።
   - የተሰበሰበውን ውኃ "ባህሮች" ብሎ በብዙ ቁጥር ጠራው፤ እንደምናውቀው አሁን ላይ ሰባት ውቂያኖሶች አሉ። በሰዓቱ ደግሞ እንዲሁ የተወሰኑ የሚታወቁ ይኖራሉ፤ ለምሳሌ በቀጣይ ምዕራፍ የምናገኛቸው ገነትን የሚያጠጡ የተባሉ አራቱ ወንዞች። ምንም እንኳን የተለያዩ ባህሮች ቢኖሩም መነሻቸው ወይም መሰረታቸው አንድ ነው። ስለዚህ ሙሴ በአንድ ሥፍራ እንደተጠራቀመ ይናገርና መለስ አድርጎ ደግሞ ባህሮች ብሎ ከፋፍሎ ይነግረናል።[24]

11. እግዚአብሔርም "ምድር በየዘሩ በየወገኑና በየመልኩ ዘር የሚሰጥ ቡቃያን፣ በምድርም ላይ በየወገኑ ዘሩ በውስጡ የሚገኘውንና ፍሬ የሚያፈራውን ዛፍ ታብቅል" አለ፤ እንዲሁም ሆነ።
   - ጸሃይ በአራተኛው ቀን ሊፈጠር፤ አስቀድሞ በሦስኛው ቀን አዝርእትን አበቀለ። ሕይወት የሚገኘው ከጸሃይ ነው የሚሉ ስሁታንን ይታደግ ዘንድ እግዚአብሔር ይህንን አደረገ።
   - የብስ ብቻ ሆነን የምንቀር አይደለንም ይልቁንም ስንፍናን ከእኛ አርቀን በተጋድሎ የእግዚአብሔርን ጸጋ አጋዥ አድርገን ፍሬን የምናፈራ ምድር እንሆናለን እንጂ።

12. ምድርም በየዘሩ፣ በየወገኑና በየመልኩ የሚዘራ ቡቃያን፣ በምድር ላይ በየወገኑ ዘሩ በውስጡ የሚገኘውንና ፍሬ የሚያፈራውን ዛፍ አበቀለች። እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደሆነ አየ።
   - ኦሪገን[25] መንፈሳዊ ትርጓሜውን ይቀጥላል፡ ማንም ሰው በራሱ ድካም ደረቅ መሬት ሆኖ ቢቀርና ፍሬን በማፍራት ፈንታ እሾህና ኩርንችትን ቢያበቅል ለማገዶነት እንደሚውል ጭራሮ ለእሳት ይሰጣል፤ ከላይ እንዳልነው ብንጋደልና መልካሙን ፍሬ የምንፋራ ምድር ሆነን ፍሬን ብንሰጥ ከአምላካችን ከእግዚአብሔር በእርግጠኝነት የምንጠብቀው ነገር ይኖራል እርሷም ወተትና ማር የምታፈሰዋ ምድር[26] ሰማያዊት ከነዓን ናት። የሃዋርያውም ቃል በእኛ ይፈጸማል "ብዙ ጊዜ በእርስዋ ላይ የሚወርደውን ዝናብ የምትጠጣ መሬት፥ ለሚያርሱአትም ደግሞ የምትጠቅምን

[21] Ibid (ref 12)
[22] ዮሃ 3:20
[23] መዝ 33፡15 ፣ 1ጴጥ 3፡12
[24] Fr Tadros Y. Malaty, commentary on genesis
[25] Ibid hom 1:2, 3
[26] ዘጸ 3:8

አትክልት የምታበቅል፥ ከእግዚአብሔር በረከትን ታገኛለችና፤ እሾህና ኵርንችትን ግን ብታወጣ፥ የተጣለች ናት ለመረገምም ትቀርባለች፥ መጨረሻዋም መቃጠል ነው።”[27]

- ምድር ፍሬ የሚያፈራውን ዛፍ አበቀለች ይህም ልባችን ነው መልካም ሰው ከልብ መልካም መዝገብ መልካሙን ያወጣልና።[28] ይህ ነገር በእኛ ቢጸና መልካም ልብን ይዘን ብንዓዝ የሁላችን ምድር እንደየ አቅሙ አንዱም መቶ፥ አንዱም ስድሳ፥ አንዱም ሠላሳ ፍሬ ይሰጣል።[29]

13. ማታም ሆነ፤ ንጋትም ሆነ። ሦስተኛም ቀን ሆነ።
   - በዚህ ቀን አራት ፍጥረታት ተፈጥረዋል።[30] ስለዚህም ቀን ሦስት ፍጥረት አስራ ሁለት።
14. እግዚአብሔርም አለ “በምድር ላይ ያበሩ ዘንድ በቀንና በሌሊትም ይለዩ ዘንድ ብርሃናት በሰማይ ጠፈር ይሁኑ ለምልክቶች፣ ለዘመናት፣ ለዕለታት፣ ለአመታትም ይሁኑ።
15. በምድር ላይ ያበሩ ዘንድ በሰማይ ጠፈር ለማብራት ይሁኑ” እንዲሁም ሆነ።
   - ምድርና ሰማይ የተባለ ጠፈርን ካዘጋጀ በኋላ ምድርን ብቻ በአዝርእት ባርኮ የቀረ አይደለም፤ በሰማይ ጠፈር ላይም ደግሞ እንዲሁ ብርሃናትን አደረገ። ለእኛ ይጠቅሙ ዘንድ ብርሃናትን ፈጠረ፤ ቀንና ሌሊቱን እንዲለዩ፤ ዘመናትን፣ አመታትን፣ ቀናትንም ይናገሩ ዘንድ ተዘጋጁ።
16. እግዚአብሔርም ሁለት ታላላቅ ብርሃናትን ፈጠረ፤ ትልቁ ብርሃን ቀንን እንዲመግብ፤ ትንሹም ብርሃን ከከዋክብት ጋር ሌሊትን እንዲመግብ አደረገ።
   - በቀን ያበራ ዘንድ ትልቁ ብርሃን የተባለ ጸሃይን ፈጠረ፤ ሌሊትንም ከከዋክብት ጋር ይመግብ ዘንድ ጨረቃን ፈጠረ።
   - አሪገንም[31] እውነተኛው ጸሃይ (“ጸሃየ ጽድቅ”[32]) የተባለው መድሃኒታችን ኢየሱስ ነው፤ ጨረቃም ቤተ ክርስትያን ናት ይላል። ጨረቃ ብርሃንን ከጸሃይ ወስዳ እንደምታበራ፤ ጨለማውንም እንደምትገልጥ፤ ቤተ ክርስትያን ከእውነተኛው ብርሃን ከኢየሱስ ብርሃንን በመውሰድ የአለምን ጨለማ ገልጣ ለሁሉ ታበራለች(ማንም ወደዝች ብርሃን ቢመጣ በክርስቶስ ኢየሱስ ብርሃን ይመላለሳል እንጂ በጨለማ አይኖርም)። ጌታ እግዚአብሔር “ወደ እኔ ተመለሱ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለው”[33] ይላልና አማኞችም እውነተኛ ጸሃይ ወደተባለው ጌታ ኢየሱስ ራሳቸውን ከፍ እያደረጉ እየቀረቡት ሲሄዱ በብርሃኑ የበለጠ እየረኩ እየተደሰቱ ይሄዳሉ። እነሱም ደግሞ የበለጠ የሚያበሩ ከዋክብትን እየሆኑ ይሄዳሉ። ኮከብ መንገድን ይመራል ይጠቁማል፤ እንደኮከብ የሚያንጸባርቅ ክርስትያንም የእግዚአብሔርን መንገድ ላጡ መሪ ይሆናል። ኮከብ እንደ ኮከብነቱ በምድር ላይ የሚያበራው በላይ በሰማይ እስካለ ነው፤ ወደ ምድር ከወደቀ ግን ለምድር ብርሃንን በመስጠት ፈንታ ጉዳትን ያመጣል። ኮከብ ክርስትያንም ብርሃን የሚሆነው ሰማይዊ እስከሆነ ድረስ ነው፤ ሃዋርያው ጳውሎስ “እኛስ ሃገራችን በሰማይ ነው” እንዳለ። ወደ ምድር ብንወድቅ ግን ምን ጥቅም እንሰጣለን..?? ለሌላውም ማሰናከያ እንሆናለን። ማንም አማኝ ከእርሱ ከክርስቶስ ጋር በመሆን እስከ ጫፍ ተራራ እንደ ጴጥሮስ፣ ያዕቆብና ዮሃንስ ቢወጣ የክርስቶስን ብርሃን ብቻ የሚያጣጥም አይደለም፤ የአባቱንም ድምጽ ነው እንጂ።
17. እግዚአብሔርም በምድር ላይ ያበሩ ዘንድ በሰማይ ጠፈር አኖራቸው።

---

[27] ዕብ 6:7-8
[28] ሉቃ 6:45
[29] ማቴ 13:8
[30] ኩፋሌ 2:12
[31] Ibid hom 1:7
[32] ሚል 4:2
[33] ዘካ 1:3

18. መአልትንና ሌሊትንም እንዲመግቡ፤ በመአልትና በሌሊትም መካከል እንዲለዩ። እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደሆነ አየ።
19. ማታም ሆነ፤ ንጋትም ሆነ፤ አራተኛ ቀን።
   - በአራተኛው ቀን ሦስት ፍጥረታት ተፈጥረዋል። ቀን አራት ፍጥረት አስራ አምስት።
20. እግዚአብሔርም አለ "ውኃ ሕይወት ያለቸውን በምድር የሚሳቡ እንስሳትን እና ከምድር በላይ በሰማይ ላይ የሚበሩ ክንፍ ያላቸው አዕዋፍን ታስገኝ" እንዲሁም ሆነ።
   - የመጀመሪያዎቹ ደመ ነፍስ ያላቸው ህያው የሆኑ ፍጥረታት ከውኃ ተገኙ። ይህም ውኃ የጥምቀት ምሳሌ ነው። አውግስጢኖስ[34] ውሃ በምድር የሚሳቡ እንስሳትን አስገኘች የሚለውን ሕዝበ እስራኤል የኤርትራ ባህር ተከፍሎ ህያው ሆነው(ሳይሞቱ) ከመውጣታቸው ጋር ያገናኘውና ይህም ደግሞ ሃዋርያው ጳውሎስ "አባቶቻችን ሁሉ ደመና ጋረዳቸው፤ ሁሉም በባህር ተሻገሩ፤ ከሙሴም ጋር ይተባበሩ ዘንድ በባሕርና በደመና ተጠመቁ"[35] ይላልና ከውኃ ሕይወት ያላቸው ሆነው መገኘታቸው እኛ በጥምቀት በኩል ሕይወት የማግኘታችን ምሳሌ እንደሆነ ያስረዳል።
   - አንድም ኦሪገን[36] እንደሚተረጉመው፡ በምድር የሚሳቡ ፍጥረታት የሃጢዓት ሃሳብ ምሳሌ፤ በላይ በሰማይ የሚበሩት ደግሞ የጽድቅ(መልካም) ሃሳብ ምሳሌ። ከውሃ ተገኙ፤ ክፉም መልካምም ከልብ እንዲገኝ። ከልባችን መዝገብ የሚወጣውን ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል እየመዘንን በክርስቶስ ኢየሱስ ብርሃን ክፉና መልካሙን እንለያለን። በዚህም ራሳችንን በምድር ከሚሳቡት እንለያለን። ለምሳሌ ወደ ሴት አይተን ከተመኘን እርሱ በውስጣችን ያለ መርዛማ ተሳቢ ነው። በልባችን መልካም መዝገብ ካለ ግን ምንም እንኳን የግብጽ አመንዝራ[37] እጅጉን አይኗን ብትጥልብን ወፍን እንሆናለን ልብስንም በጇ ጥለን ጥለናት ወደ ውጭ እንበራለን።
21. እግዚአብሔርም ታላላቅ አንበሪዎችን፣ ውኃ ያስገኘውን ተንቀሳቃሽ ሕያው ፍጥረትን ሁሉ በየወገኑ፤ የሚበርሩ አዕዋፍንም ሁሉ በየወገናቸው ፈጠረ። እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደሆነ አየ።
   - ሁሉም በየወገናቸው ተፈጠሩ፤ እዛው ውሃ ውስጥ የቀሩ አሉ እንደ አሳ፣ በርረው ወጥተው የቀሩ አሉ እንደ ወፍ፣ ደግሞ አንዴ ከውኃው አንዴ ከምድሩ የሚሉ አሉ እንደ እንቁራሪት። ይህም ምሳሌ ነው፡ ባሕር የጥምቀት፤ በባሕሩ ጸንተው የቀሩት በክርስትናቸው ጸንተው የሚኖሩ ሰዎች ምሳሌ፤ በረው በረው የሄዱት ወደ ምንፍቅና ወደ ሃጢዓት ላይመለሱ የሄዱ ሰዎች ምሳሌ፤ አንድ ጊዜ ወደ ምድር አንድ ጊዜ ወደ ባሕር የሚመላለሱ፤ አንድ ጊዜ ወደ ሃይማኖት ወደ ጽድቅ አንድ ጊዜ ወደ ምንፍቅና ወደ ሃጢዓት የሚመላለሱ ሰዎች ምሳሌ ነው።[38]
   - አንድም "መለካም ነው" ተብሏልና ባህር የዓለም ምሳሌ፤ በባህር ጸንተው የቀሩት በዓለም ውስጥ ሆነ ግን ደግሞ በጌታ ኢየሱስ መንገድ የሚጓዙ ሰዎች ምሳሌ፤ ከባህር በርረው በርረው ወጥተው የቀሩት ከዓለም ሙሉ በሙሉ ተለይተው ወጥተው ወደ ምናኔው ወደ ምንኩስና ወደ ገዳም ሕይወት የበረሩ ሰዎች ምሳሌ፣ አንዴ ከባህሩ አንዴ ከምድሩ የሚሉት ደግሞ ወደ ገዳም እየሄዱ በረከትን የሚቀበሉ ከዛም ደግሞ ወደ ዓለም የሚመለሱ ሰዎች ምሳሌ ነው።[39]

[34] Augustine on psalms 81:9-11
[35] 1 ቆሮ 10፡1-2
[36] On genesis hom 1:8
[37] ዘፍ 9፡7-12
[38] ዘፍጥረት አንድምታ
[39] Ibid

- አሪገን[40] ተሳቢዎችን የሃጢዓት ሃሳብ ምሳሌ ብሎ ከፈታ በኋላ "እግዚአብሔር የሚበርሩትንም የሚሳቡትንም በአንድነት መልካም እንደሆኑ ከተናገረ እንዴት ተሳቢን ከክፉት ጋር እናገናኛለን በማለት የሚጠይቅ ሰው ይኖራል" በማለት ጥያቄ አንስቶ ሲመልስ "እነርሱም ቢሆን ለእኛ መልካሞች ናቸው ምክንያቱም ብዙ ዋጋን ያሰጡናል ያስሽልሙናልና፤ ሰይጣን ያንን ሁሉ ክፉ ነገር ስላደረገበት ነበር ኢዮብ በእጥፍ የተባረከው፤ ሃዋርያው ጳውሎስም "ማንም ቢሆን እንደ ህጉ ካልታገለ አክሊልን አያገኝም" እንዲል ጥንቁቆች ሆነን ብንጓዝ ሁሉም ነገር ለእኛ ለመልካም ነው ስለዛ "መልካም እንደሆነ አየ" አለ" ይላል።

22. እግዚአብሔርም እንዲህ ብሎ ባረካቸው "ብዙ ተባዙ የባህርንም ውኃ ሙሏት፤ ወፎችም በምድር ላይ ይብዙ።"
23. ማታም ሆነ ንጋትም ሆነ አምስተኛ ቀን።
    - ዕለት አምስት ፍጥረት አስራ ስምንት።
24. እግዚአብሔርም አለ "ምድር ሕያዋን ፍጥረታትን እንደ ወገኑ፤ እንስሳትንና ተንቀሳቃሾችን የምድር አራዊትንም እንደወገኑ ታውጣ" እንዲሁም ሆነ።
25. እግዚአብሔርም የምድር አራዊትን እንደየወገኑ፤ እንስሳትንም እንደየወገኑ፤ በምድር የሚንቀሳቀሰውንም ሁለ እንደየወገኑ አደረገ። እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደሆነ አየ።
    - የምድር አራዊትን ሁሉ በየወገኑ ፈጠረ። ሁሉም ሲፈጠሩም መልካም ሆነው ተፈጠሩ። አሁን ላይ ሰውን የሚተናኮሉ እንሰሳት አስቀድሞ እንዲህ አልነበሩም፤ ሰው ባለመታዘዙና በማመጹ እነሱንም አመጸኞች አደረጋቸው ይላል ቴዎፍሎስ።[41] አሁንም ቢሆን ሰው ከክፉት ሁሉ ርቆ ሙሉ በሙሉ ወደ በፊቱ ማንነቱ ቢመለስ እንሰሳቱም ወደ በፊት ማንነታቸው ይመለሳሉ ለሰውም ተገዢ ይሆናሉ። ለዚህም ማስረጃ አባታችን አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ናቸው፤ ከአናብስትና አናብርት ጋር ያለምንም ጸብ የኖሩ በምልጃቸው ሁሌም የምንጠቀምባቸው ታላቅ አባት ናቸው። ሌላው ከእንሰሳት ጋር የኖሩት የቅርብ ጊዜው አባት ኢትዮጵያዊው አባ ገብረ ክርስቶስ ናቸው፤ ግብጽ ውስጥ በስፋት ይታወቃሉ።[42]
26. እግዚአብሔርም አለ "ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር፤ የባሕር አሳዎችንና የምድር አራዊትን፤ የሰማይ ወፎችን፤ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፣ በምድርም ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዛ"
    - እግዚአብሔር አምላክ ፍጥረታትን ሁሉ ፈጥሮ ከጨረሰ በኋላ ሰውን ፈጠረው። ሰው የተፈጠረው በስድስተኛው ቀን ነው፤ ክርስቶስ መድኅንም ሰውን እንደ አዲስ የፈጠረው ከሞት ወደ ሕይወት የመለሰው በስድስተኛው ቀን (አርብ) በስድስት ሰዓት ነበር። አውግስጢኖስ[43] ከአዳም ጀምሮ ያለውን ዘመን በመከፋፈል፤ መድኅን ዓለም ክርስቶስ ሲመጣም በስድስተኛው ዘመን ላይ እንደመጣም ያምናል። ዘመናቱም፦ አንደኛው ከአዳም እስከ አብረሃም፤ ሁለተኛ ከአብረሃም እስከ ኖህ፤ ሦስተኛ ከኖህ እስከ ዳዊት፤ አራተኛ ከዳዊት እስከ ባቢሎን ምርኮ፤ አምስተኛ ከባቢሎን ምርኮ እስከ ዮሃንስ መጥምቅ፤ ስድስተኛው አሁን እኛ ያለንበት ዘመን እስከ ዳግም ምጽአት ድረስ ነው። ክርስቶስም በዚህ ዘመን መጣ ዳግም ደግሞ ይመጣል፤ እርሱም ሰባተኛው ዘመን ነው። እግዚአብሔር አምላክ ፍጥረታትን ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን አረፈ እንዲል ሰባተኛው ዘመን የጌታ

[40] On genesis 1:10
[41] To Autolycus 2:17 on the sixth day
[42] Tadros Y. Malaty, on Genesis
[43] On Psalm 93

እረፍት የሚባለው ነው እርሱም ዘላለማዊ ነው። በስድስተኛው ዘመን እንደ አዲስ ፈጥሮናል፤ ዳግም ሲመጣም ደግሞ ወደ እረፍቱ ያገባናል። አሜን።

- "እግዚአብሔርም ሰውን '**እንፍጠር**' አለ" የሚለው አነጋገር ሌሎች ፍጥረታት ላይ ያላየነው አነጋገር ነው። ከላይ ተመልክተን እንደመጣነው "እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰማይና ምድርን **ፈጠረ**" ይላል እንጂ ለሰው በተነገረው መልኩ ልፍጠር አይልም፤ ሰውን ቀጥታ ፈጠረ በማለት ፈንታ ሰው ያለውን ክብር ሲያመለክት "እንፍጠር" ይልና ነው ከምድር አፈር የሚያበጀው። ወይም ደግሞ እንደ ብርሃን፣ ጠፈር እና በጠፈር ላይ እንዳሉ ብርሃናትም "ይሁን" አላለም፤ እንደ እንስሳትም ምድር ሰውን ታውጣ አላለም፤ ግን ደግሞ ለሰው የሚጠቅመውን ነገር ሁሉ ካዘጋጀ በኋላ በሁሉም ላይ ይሾመው ሁሉን ይገዛ ዘንድ ሰውን "እንፍጠር" አለ።
- ሌላው የሰው ተፈጥሮ ላይ ትልቁ ነገር እግዚአብሔር አምላክ ሥላሴነቱን ገልጦ መናገሩ ነው። ሌሎች ፍጥረታት ላይ ያልተገለጠ ነገር ሰው ላይ ግን እግዚአብሔር በአንድነቱ በሦስትነቱ ሰውን ፈጠረው። "እግዚአብሔርም አለ 'ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር..'" የሚለውን ቃል ስንመለከት "እግዚአብሔርም አለ" ማለቱ አንድነቱን "በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር" ብሎ ደግሞ አብዝቶ መናገሩ ሦስትነቱን ያመለክታል። "እንፍጠር" ብሎ አንድ ሰውን በመፍጠሩ አንድነቱን ሲያመለክት፤ በብዙ አንቀጽ መናገሩ በራሱ ደግሞ ሦስትነቱን ያመለክታል። ስለዚህ በአጭሩ ሥላሴ በአንድነት ፈጠሩ ማለት ነው።
- የሥላሴ አስተምህሮ በብሉይ ኪዳን ምስጢር ነበር፤ ይህ ምስጢር የሆነው ነገር ግን በሃዲስ ኪዳን ተገልጦ እንመለከተዋለን። በእዚህ ምዕራፍ ቁጥር አንድ ላይ የተመለከትነው "እግዚአብሔር(አብ) በመጀመሪያ(ወልድ) ሰማይና ምድርን ፈጠረ...የእግዚአብሔርም መንፈስ(መንፈስ ቅዱስ) በውኃው ላይ ሰፍፎ ነበር።" የሚለው የስላሴ ምስጢራዊ መገለጥ በሃዲስ ኪዳን ሲገለጽ ዮሃንስ እንዲህ አለ፡ "በመጀመሪያ ቃል(ወልድ) ነበረ፤ ቃልም(ወልድም) በእግዚአብሔር(አብ) ዘንድ ነበረ፤ ቃልም(ወልድም) እግዚአብሔር ነበረ። ይህም በመጀመሪያ በእግዚአብሔር(መንፈስ ቅዱስ) ዘንድ ነበር።"
- ሌላው ደግሞ እጅጉን የሚያስደንቀንና እግዚአብሔር አምላክ ለሰዎች ያለውን ፍቅር የምንረዳው በራሱ መልክና ምሳሌ በመፍጠሩ ነው። ይህም የአምላክ መልክ ውስጣዊው የማይታየው ሰዋችን እንጂ ሟቹ ሰዋችን አይደለም ይላል ኦሪገን።[44]
- ጌታ ኢየሱስ ለቄሳር ግብር ስለመክፈል ጥያቄ ሲቀርብለት የመለሰው መልስ እንዲህ የሚል ነበር፡ "'በገንዘቡ ላይ ያለው መልኩ፤ ጽህፈቱስ የማን ነው?' አላቸው። እነርሱም የቄሳር አሉት፤ ክርስቶስም 'እንግዲያውስ የቄሳርን ለቄሳር የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር ስጡ' አላቸው።"[45] በገንዘቡ ላይ የታተመው የቄሳር መልክ ነው፤ በእኛ ላይ ደግሞ የእግዚአብሔር መልክ ነው የታተመው በነፍሳችን። ስለዚህም የቄሳር መልክ ያለበትን ለቄሳር፤ የእግዚአብሔር መልክ ያለበትንም ለእግዚአብሔር ልንሰጥ እንደሚገባ ሲያስረዳ የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ስጡ ይላል። እርሱ ከሰጠን ሌላ ትርፍ ከእኛ የሚፈልግ አይደለም፤ ግን ደግሞ የሰጠንን መልክ መልሰን እንስጠው፤ ከራሳችን የሆነ ሌላ እንስጠው ብንል ሃጢዓትን ነው የምንሰጠውና የሰጠንን የራሱን መልክ መልሰን እንስጥ.. በማለት አውግስጢኖስ ያብራራል።[46]

27. እግዚአብሔርም ሰውን በእግዚአብሔር አምሳል ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው።

---

[44] On Genesis hom 1:13
[45] ማቴ 22፡20
[46] On Psalm 67

- እግዚአብሔር አምላክ ሰውን በአምሳሉ ፈጥሮ ከሌሎች ፍጥረታት ሁሉ ለይቶ የበላይ አደረገው። ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው።
- ሴት አሁን አልተፈጠረችም ግን ደግሞ በአዳም ሥጋና አጥንት ውስጥ አለችና፤ ከእርሱም ደግሞ የምትገኝ ናትና አንድ ላይ ተናገረ። ቀጠል አድርጎ ብዙ ተባዙ ብሎ እንዲባርካቸው ወንድ ብቻውን ሊበዛ ሊራባ አይችልም ሴትም እንዲሁ፤ ቅድስት ድንግል ማርያም ልጅ እንደምትወልድ ስትበሰር "ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል?" ነበር ያለችው፤ ሴትም ያለ ወንድ፤ ወንድም ያለሴት.. ልጅ እንዳይወልዱ እንዳይባዙ አውቆ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው።

28. እግዚአብሔርም ባረካቸው እንዲህም አላቸው "ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት፤ ግዟትም፤ የባህርን አሳዎችንና የምድር አራዊትን፤ የሰማይ ወፎችንና እንስሳስትንም ሁሉ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዟቸው።"
   - ልጅን መውለድ ከውድቀት በኋላ የመጣና የሃጢዓት ውጤት ሳይሆን ከእግዚአብሔር የተሰጠ ጸጋና በረከት ነው።
   - በሁሉ ላይም ገዢ አደረጋቸው። እግዚአብሔር አምላክ በባህሪው[47] ሁሉን ይገዛል፤ ሰውን ደግሞ በራሱ አምሳል ፈጥሮ በጸጋ የሁሉ ገዢ አደረገው።
   - ኦሪገን[48] እግዚአብሔር ሰውን በአምሳሉ መፍጠሩንና ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው የሚለውን ሲተረጉም፡ የእግዚአብሔር አምሳል ውስጣዊ ነገር ነው፤ ሰው ደግሞ በውጭ ከሚታየው ሥጋው ሌላ ነፍስና መንፈስ አለው፤ ወንድና ሴትም የመንፈስና የነፍስ ምሳሌ ነው ይላል። ወንድና ሴት አንድ በመሆን በህብረት ብዙ ፍሬን እንደሚያፈሩ ልጆች እንደሚኖራቸውና እንድሚበዙ ነፍስና መንፈስም እንዲሁ ነው። ነፍስ ወደ ሥጋ ሳይሆን ወደ መንፈስ በማድላት ከመንፈስ ጋር አንድ በመሆን በህብረት ቢሰሩ ብዙ የመንፈስ ፍሬዎችን ማፍራት ይጀምራሉ። "ምድርንም ግዟት" ይላልና ሥጋን በመግዛት ይኖራሉ ማለት ነው። እውነተኛ ክርስትያን በሥጋው ላይ ንጉስ ሆኖ ሥጋውን መግዛት የሚችል ነው። ነገር ግን በተቃራኒው ባል በሚስት ላይ ሚስትም በባሏ ላይ ቢያመነዝሩስ..?? ይህ አይነቱ ከእግዚአብሔር በረከት የተለየ ድርጊት ፍሬውም የአመጽ ነው፤ የገዥነትም ስልጣን በእነርሱ ዘንድ የለም፤ ይልቁን መጨረሻቸው ጥፋትና ቅጣት ነው። መጽሃፍ እንደሚናገር "የአመንዝራዎች ልጆች ግን ከቁጥር የጎደሉ ይሆናሉ። ከሕግ ተላላፊ መኝታም የተወለደ ልጅም ይጠፋል።"[49] በማለት ኦሪገን ነፍስም ከመንፈስ ተልይታ ወደ ሥጋ ፍቃድ ብትወድቅ ፍሬን ልታፈራ አትችልም (ፍሬው የአምጽ ነው፤ እሾህና ኩርንችት ነው) ይላል።

29. እግዚአብሔርም አለ "እነሆ መብል ይሆናችሁ ዘንድ በየዘሩ የሚዘራውንና የሚበቅለውን በምድር ሁሉ ላይ የምትዘሩትን የእህል ፍሬ፤ ዘሩ በውስጡ ያለውን ቡቃያ፤ በየፍሬውም የሚዘራውን ዛፍ ሁሉ ሰጠኋችሁ፤

30. ለምድር አራዊት ሁሉ፤ ለሰማይም ወፎች ሁሉ፤ ሕያው ነፍስ ላላቸው ለምድር ተንቀሳቃሾች ሁሉ ሃመልማሉ ሁሉ መብል ይሁንላችሁ።" እንዲሁም ሆነ።
   - እግዚአብሔር በምድር ላይ ከፈጠረው ከእህል ፍሬ ሁሉ ለእንስሳትም ለሰውም መብል ይሆን ዘንድ ሰጠ።

31. እግዚአብሔርም የፈጠረውን ሁሉ እጅግ መልካም እንደሆነ አየ። ማታም ሆነ ንጋትም ሆነ ስድስተኛ ቀን።

---

[47] በባህሪው ማለት ሰጪ የሌለበት ለማለት እንጂ እግዚአብሔርስ በባህሪው እንዲህ ነው ተብሎ የሚነገር አምላክ አይደለም። በባህሪው ማንም አያውቀውም፤ ከሰውና ከመላእክት አንደበት፤ ከቃላት ሁሉ በላይ ነው።

[48] On Genesis 1:15

[49] ጥበብ 3፡16

- እግዚአብሔር አምላክ የፈጠረውን ፍጥረት “መልካም እንደሆነ አየ” እያለ እንደመጣ ከላይ አስተውለናል፤ አሁን ግን መልካም ብቻ አይደለም ይልቁንም “እጅግ መልካም” እንደሆነ አየ ተባለ።
- በስድስተኛው ቀን ሁለት ፍጥረታት ተፈጥረዋል አጠቃላይ ሃያ ሁለት ፍጥረታት።

ታድያ ከዚህ ሁሉ በኋላ በሰባተኛውም ቀን አረፈ ተባለ “እግዚአብሔር ሰባተኛዋን ቀን ባረካት፤ ቀደሳትም፤ ሊፈጥረው ከጀመረው ሥራ ሁሉ በእርሷ አርፏልና።” እንዲል በምዕራፍ 2፡3 ላይ ሰንበት ሆነች ባረካትም።

- በሰንበት አረፈ መባሉ ጌታ የሚደክመውና የሚያርፍ አምላክ ሆኖ ሳይሆን እኛ ከሥራ ሁሉ እናርፍባት ዘንድ ቀድሶ ሲሰጠን ነው። የክርስትያኖች ዋናው እረፍታችን ክርስቶስ ነውና የምናርፈው በእርሱ ነው። እርሱ ሰንበታችን ነው።
- አውግስጢኖስ ዘመናትን በሰባት ከፍሎ እንመለከታለን.. ይከውም ከአዳም እስከ ኖህ (1ኛ ዘመን) ከኖህ እስከ አብረሃም(2ኛ ዘመን)፣ ከአብረሃም እስከ ዳዊት(3ኛ)፣ ከዳዊት እስከ ባቢሎን ምርኮ(4ኛ)፣ ከባቢሎን ምርኮ እስከ ዮሃንስ መጥምቅ(5ኛ)፣ ከዮሃንስ መጥምቅ በኋላ ጌታ መጣ ከጌታ ጀምሮ እስከ ዳግም ምጽአት አሁን ያለንበትን ጨምሮ ማለት ነው(6ኛ) እና ከዳግም ምጽአት በኋላ ያለውን ዘላለማዊ ሕይወት ሰባተኛ ዘመን በማለት ይከፍለዋል። ሰባተኛው ማብቂያ ስለሌለው በሥነፍጥረት ላይም ሰባተኛው ቀን ላይ “መሸም ነጋም” የሚል ቀን አናገኝም።

ፍጥረታትን ለብቻው ለፈጠረ፤ ሰውን ደግሞ ከሁሉ አልቆ አብልጦ በአርአያው ለሰራ አንድ አምላክ ለሚሆን ለእርሱ ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ክብርና ምስጋና ሁሉ ይሁን።[i]

---

[i] ምናልባት ጥያቄ የፈጠረባችሁ ነገር ቢኖር በቴሌግራም http://t.me/aklil1 ላይ ታገኙኛላችሁ
ቻናሎቻችንን ለመቀላቀል http://t.me/hamongog2 http://t.me/orthodoxapologetics
ለwebsite www.orthoapologetics.wordpress.com